# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 155 ሚያዝያ 27 2003 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እህቶችና እናቶች ትግሉን በሰፋት እንዲቀላቀሉ ጥሪ ያደርጋል። በንቅናቄያችንም ሆነ እኛ ተሳትፎ በምናደርግባቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለሴቶች ምቹ የሆኑ አደረጃጀቶችን ለመከተል እንሞክራለን፤ ይህንን ደግሞ ያለማቋረጥ ማጎልበት አፈልጋለን። ስለሆነም እህቶችና እናቶች በትግላችን በንቃት ተሳተፉ፤ አብረን እንታገል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግብጽ ውስጥ በህዝብ የተመረጠ መንግሥት እስኪመሠረት የአባይ ግድብ ግንባታ እንደሚዘገይ ቪ ኦ ኤ ዘገበ

ከሰሞኑ በአባይ ግድብ ስም ከደሃዉ ኢትዮጵያዊ ገንዘብ ሲሰበሰብ የሰነበተዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ግብጽ የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች የወንዙን ውሀ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ባደረጉት የመሰረተ-ሃሳብ ስምምነት ለመደራደር እንድትችል ስምምነቱን የማጽደቁን ጉዳይ አዲስ የግብጽ መንግስት እስከሚመሰረትበት ጊዜ ድረስ ለማዘግየት ኢትዮጵያ ተስማምታለች ሲል የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ዘገበ። እንደ አሜሪካ ድምፅ ዘገባ "ኢትዮጵያ የወቅቱን የግብጽ ሁኔታ ስለምታጤን የራሳቸውን መንግስት መስርተው ፕረዚዳንታቸውን በዲሞክራስያዊ ሂደት እስከሚመርጡበት ጊዜ ድረስ ለግብጽ ጊዜ መስጠቱን እንደ ብልህነትና አስተዋይነት አድርጋ ታየዋለች።" በማለት በግብጽ የወያኔ አምባሳደር መሐሙድ ዲሪር ጌዲ መናገሩን ይሄው ዘገባ አሳይቷል።

ወያኔ በመጪው 5 አመት እሰራዋለሁ በማለት ይፋ ባደረጋቸው የልማትና የእድገት ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዝርዝሮች ውስጥ ፍጽሞ ያልተካተተዉን ይህንን የመሰለ ትልቅ አቅም የሚጠይቅ ግንባታ ያለምንም መሰናዶ ለህዝብ ይፋ ማድረጉ ቀድሞውንም ቢሆን የኢትዮጵያን ህዝብ የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሆን ብሎ የፈጠረዉ ግርግር እንደሆነ ብዙዎች (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በደል ደረሰብን ያሉ የመቀሌ ከተማ ነዋሪዎች አመጹ፣ የወያኔ ፖሊሶች ሰልፉን ለመበተን ሃይል መጠቀማቸውም ተሰማ

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት በመቀሌ ከተማ ዙርያ በሚገኘው የእንደርታ ወረዳ ውስጥ በሕገወጥ ተገንብተዋል የተባሉትን ከአራት ሺሕ በላይ ቤቶች ለማፍረስ ያደረጉት እንቅስቃሴ ከመቀሌ ከተማ ነዋሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ እንደገጠመው ተገለጸ:: የህዝብን ተቃዉሞ በድብደባና በእስር ብከዚሁ ከመቀሌዉ አመጽ ጋር በተያያዘ ተቃውሞውን አስተባብረዋል ያላቸዉን 15 ሰዎች ለእስር እስር ቤት ከመወርወሩ ባሻገር የዘረኛዉ አገዛዝ በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ የኃይል ዕርምጃ እየተወሰደ መሆኑን የዓይን እማኞች ጠቁመዋል:: በተላይ በመቀሌ ከተማ ዙርያ ልዩ ስሙ ማይ አንበሳ በተባለ አካባቢ እንደተገነቡ የሚነገርላቸውን ከአራት ሺሕ በላይ ቤቶች ለማፍረስ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የየተደረገ ውን ሙከራ ነዋሪዎቹ አጥብቀዉ በመቃወማቸው ፖሊስ ጣልቃ መግባቱን ከወደ መቀሌ የሚደርሱ ዜናዎች ያስረዳሉ።

በተለይም በአካባቢው የሚገኘው የፌዴራል ፖሊስ ንብረታችንን አናስነካም ብለዉ በልቅሶና በኡኡታ የወጡትን የአካባቢዉ ነዋሪዎች ለመበተን አስለቃሽ ጋዝ በመጠቀም ከፍተኛ ድብደባ አካሂዷል::፤ የአካባቢው ነዋሪዎች ተቃውሞአቸውን አናቆምም ብለዉ በመቀጠላቸው፣ ከ300 በላይ የሚሆኑት ባሎኒ በመባል ወደሚታወቀው የመቀሌ ከተማ ስታድዮም ተወስደው ታግተው ሲታገቱ ለግዜዉ ቁጥራቸዉ በዉል ተለይቶ ያልታወቀ የአካባቢዉ ሚሊሻዎች ደግሞ በሌሊት ትጥቃቸውን እንዲፈቱ ተደርጓል:: በአሁኑ ወቅት አካባቢው በከፍተኛ የፖሊስ ጥበቃ ሥር መሆኑንና በአካባቢዉ መረጋጋት እንደማይታይ ብዙ የአካባቢዉ ሰዎች ይናገራሉ።

## የተባበሩት መንግስታት ተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ርዳታ ለኢትዮጵያ እንደሚያስፈልግ ገለጸ

በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ አገልግሎት ሰጪ ዲፓርትመንት ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ባወጣው መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ላሉ ተጨማሪ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች እስከሚቀጥለው ጥቅምት ወር ድረስ የሚዘልቅ የአስቸኩአይ ጊዜ የምግብ ርዳታ ልገሳ እንዲደረግ ጥሪውን አቅርቦአል።

ዲፓርትመንቱ በዚሁ ባወጣው መግለጫ የአሁኑ አስቸኳይ ጊዜ የምግብ ርዳታ የተጠየቀው በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ ለሚገኙ አርብቶ አደሮች መሆኑንና እስካሁን ባለው ጊዜ የመጠጥ ውሃ ችግርን ለማቃለል በከባድ መኪናዎች ወደቦታው ውሃ እየተጓጓዘ መሆኑን ገልጹአል። ከዚህም በተጨማሪ በርካታ ዓለም አቀፍ ርዳታ ለጋሽ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለተወሰኑት ችግረኞች የምግብ ርዳታ በማድረግ እንዲሁም ለከብቶች ጤንነት መጠበቂያ የመድሃኒት አቅርቦት ርብርብ ላይ እንደሚገኙም አያይዞ ገልጹአል።

ይሄው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰባአዊ መብቶች ዲፓርትመንት ለኢትዮጵያዊያኑ የተጠየቀው የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ርዳታ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የፕሬስ ነጻነትን እንደሚረግጥ በታዛቢዎች ፊት በይፋ አሳየ

በየአመቱ የሚከበረው የአለም የፕሬስ ነጻነት ቀን በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ በመላው ዓለም የተከበረ ሲሆን የነጻ ፕሬስ ጠላት የሆነዉና የኢትዮጵያን ህዝብ ከሚዛናዊ መረጃ ዉጭ ጨለማ ዉስጥ አፍኖ የያዘዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝም ይህንን በአል ለማክበር አዲስ አበባ ዉስጥ ጎንበስ ቀና ሲል ተይቷል። የፕሬስ ነጻነት ቀን ለምን እንደሚከበር ያልገባቸዉ የዘረኛዉ ስርአት ባለስልጣኖች በበአሉ አከባበሩ ወቅት ውዝግብ እንዲፈጠር አድርገዉ እንደነበር አድስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የአይን ምስክሮች ተናግረዋል።

እንደ አይን ምስክሮቹ አባባል ለዚሁ ውዝግቡ የተፈጠረዉ በእለቱ ስብሰባ ላይ የተገኙት የዘረኛው ስርአት ኮሙዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ባለሥልጣናት የበአሉ አዘጋጆች ከነደፏቸዉ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ውስጥ የተወሰኑት እንዳይቀርቡ ጫና ለማሳደር ሲሞክሩ ነዉ። የእለቱን ፕሮግራም ያዘጋጁት ሆርን አፍ አፍሪካ ፕሬስ ኢንስቲቲዩት፣ የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ጋዜጠኞች ማኅበርና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጋዜጠኞች ኅብረት ከዩኔስኮ ጋር በመሆን ሲሆን ፕሮግራሙ ተነድፎና ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀው ከአንድ ሳምንት በፊት ነበር። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአባይ ግድብ ግንባታ ስም የዜጎችን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ወያኔ የሚያደርገውን ዘመቻ ወደ ዲያስፖራው ህብረተሰብ ለማዝለቅ እየተፍጨረጨረ መሆኑ ታወቀ

የዘረኛውና ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ እየናረ በመጣው የኑሮ ውድነት የተማረረውን የኢትዮጵያ ህዝብ የተቃውሞ አቅጣጫ ለማስቀየር ብቻ ሆን ተብሎ የተፈበረከውን የአባይ ግድብ ግንባታ ዜና በማሰራጨት የተጠመደው የዘረኛውና ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ ከአገሩ ወጥቶ በስደት ሰው አገር የሚኖረውን ስደተኛ ጭምር በርካሽ ፕሮፖጋንዳ ለመከፋፈል የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደቀጠለበት የዝግጅት ክፍላችን ዜና ዘጋቢዎች አስታወቁ።

በአሜሪካ የመለስ ዜናዊ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር የሆነው ግርማ ብሩ ስለ ወያኔ የ5 አመት የልማትና እድገት ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለዲያስፖራው ህብረተሰብ ለማስረዳት ተልኮ የነበረው የወያኔ መል ዕክተኛ ቡድን በደረሰበት ታላቅ ተቃውሞ በኪሳራ ወደአገሩ ከተመለሰ በኋላ ፤ የኦሮሞ ኮሚኒቲ በብዛት የሚኖርበትን የሚኒሶታ ግዛት ድረስ ዘልቆ ስብሰባ ለማድረግ ከሞከር ጀምሮ በተለያየ የዋሽንግተን ዲሲ ሬድዮ ጣቢያዎችና የዲያስፖራው ፓልቶክ ውይይት መድረኮች አገዛዙ የሚፈጽማቸውን ወንጀሎች በማስተባበልና ስለአባይ ግድብ በመስበክ ሥራ መጠመዱን ለማወቅ ተችሎአል።

በአድርባይነታቸውና በታማኝ ሎሌነታቸው ላለፉት 20 አመታት የመለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የህወሃት መሪዎች የስልጣን በረከት ከተቸሩት አንዱ የሆነው ግርማ ብሩ፤ በብርሃኔ ገብረክርስቶስም ሆነ እርሱን በተካው ካሳሁን አየለ የአገልግሎት ዘመን ሁለቱም አምባሳደሮች ያልመሰረቱትን ግንኙነት ከዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ ነዋሪዎች ማህበር ከሆነው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አዲስ አበባ ውስጥ ያለው ውጥረት እየተባባሰ ነው፣ በህብረተሰቡ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በረከቱ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እየጨመሩ መምጣታቸውንና እነኝህም ወንጀሎች ከዝርፊያ እስከ ግድያ ድረስ ያለውን እንደሚያካትቱ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ በባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ፤፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የኑሮ ውድነትን ፍጹም መቋቋም እያቃታቸው በመጣበት ባሁኑ ሰአት እንዲህ አይነት ወንጀል እየተበራከተ መምጣቱ በከተማይቱ ውስጥ ያለውን ውጥረት እጂግ ያባባሰው መሆኑንም ዘጋቢያችን በላከው ዜና አክሎ ገልጹአል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በአዲስ አበባ ህዝብ ላይ እንዲህ አይነት አይን ያወጡ ወንጀሎች በአደባባይና በጠራራ ጸሃይ እየተፈጸሙ ባለበት በአሁኑ ሰ ዓት የዘረኛው አገዛዝ ፖሊሶች በአብዛኛው ጊዚያቸውን እያጠፉ ያሉት ወጣቶች ህዝባዊ አመጽ እንዳያስነሱ በስለላ ስራ ላይ በመጠመድ መሆኑንና፣ በህብረተሰቡ እየተፈጸሙ ያሉትን በርካታ ወንጀሎ ችላ በማለት እንደሆነ ተገልጾአል።

በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች ነዋሪ የሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች ይህን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተባባሰ የመጣ ወንጀል አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ ላለ ወንጀልና ዝርፊያ ዋና መንስኤው በሃገሪቱ የሚታየት አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና፣ የማህበረሰባዊ ቀውሶች እንደሆኑና በተለይም ፍጹም ለመግፋት አስቸጋሪ እየሆነ የመጣው የኑሮ ውድነት በርካቶችን ለዝርፊያ ሊገፋፋቸው እንደሚችል ገልጸዋል። አስተያየት ሰጪዎቹ በሌላ በኩል እንደገለጹት የዘረኛው አገዛዝ በአሁኑ ሰአት እጂግ ከፍተኛ ውጥረትና ቀውስ ላይ የሚገኝ በመሆኑና በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ ይቺላል የሚለው ፍርሃቱ እያየለበት በመምጣቱ፣ ህብረተሰቡን በተለያዩ አስፈሪ ሁኔታዎች ለመጥመድ ሲል የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ከመቆጣጠር ይልቅ ቺላ ማለት መምረጡን ገልጸዋል:: (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሴቶችና ወንዶች መለስን "በቃ!" ብለን በጋራ እንነሳ!

የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶችን በአንክሮ የተከታተለ ማንኛውም ሰው ከሚገረምባቸው ነገሮች አንዱ ሴቶች ያሳዩት ቆራጥነትና እልህ እንዲሁም ያካሄዱት ብስለት የተሞላው ትግል ነው።

በቱኒዚያ የወጣቶች እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣት ሴቶች ከመጀመሪያው ጀምሮ የአመራር ቦታ በመያዝ ተሳትፈዋል። በግብጽም የወጣት ሴቶች እልህ ከወንዶቹ በልጦ ታይቷል። ዜጎቿ በኑሮ ደረጃ፣ በባህልም በትምህርትም ከሌሎች ባነሰ ደረጃ ላይ ይገኛሉ በሚባለው የመን ውስጥም ቢሆን የሴቶች ተሳትፎ እጅግ አስገራሚ ነው። በእነዚህ አገራት በተደረጉ ህዝባዊ ሰልፎች የበርካታ ህፃናትና አረጋዊያን መገኘት በአብዛኛው የሴቶች የተሳካ የቅስቀሳ ውጤት እንደሆነ መገመት ይቻላል።

የሴቶች በህዝባዊ አብዮቶች በስፋት መሳተፍ የበርካታ ሰው መሳተፍ ማለት ብቻ አይደለም። ከቁጥር ባለፈ በርካታ ተጨማሪ እሴቶች አሉት።

1. ሴቶች ከወንዶች በላይ ታጋሾች ናቸው፤ ሲያምኑ ደግሞ በቀላሉ አይመለሱም ተብሎ ይታመናል። እናም የሴቶች በተቃውሞ ትግል ውስጥ በብዛት መሳተፍ ሥርዓቱ በህዝቡ ምን ያህል እንደተጠላ አመላካች ነው።
2. የወጣት ሴቶች በድፍረት ለተቃውሞ አደባባይ መውጣት ወጣት ወንዶችን ያጀግናል። የወጣት ወንዶች መጀገን ደግሞ ወጣት ሴቶቹን ይበልጥ ያጀግናል። ወጣት ሴትና ወንዶች በእርስ በርስ አርዓያነት ይጀጋገናሉ።
3. የእናቶች መቁረጥ አባቶችን ያነሳሳል፤ የእናትም የአባትም መነሳት ደግሞ መላው ቤተሰብ በሥርዓቱ ላይ እንዲነሳ ያደርገዋል።
4. የሴቶች በትግል አመራር ቦታ ላይ መገኘት በተቃዋሚዎች መካከል ህብረትን፣ መተሳሰብን ባጠቃላይም ቤተሰባዊ ስሜት ይፈጥራል።
5. ሴቶችና ወንዶች በእኩል የተሳተፉበት ትግል ድል የማድረግ እድሉ ከፍተኛ ነው። ማንኛውም ወገን የመሸነፍን እፍረት መሸከም አይፈልግም!!!
6. ሴቶችና ወንዶች አብረው ሲቆሙ ነው የኅብረት ጥቅም በጉልህ የሚታየው!

እኛ ኢትዮጵያውያን በቃ-ጋዮ ብለን በቅርቡ መነሳታችን አይቀሬ ነው። ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች በእንደዚህ ዓይነት ወቅት የሴቶች ሚና ከወንዶቹ በላይ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

በህዝባዊ አብዮቶች ወቅቶች ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ጊዜ የሴቶች ንቁ ተሳትፎ የመላው ማኅበረሰብ የተሳትፎ ጥልቀት መለኪያ ነው። ዲሞክራሲ የወንዶችን ተሳትፎ ብቻ ማጎልበት ማለት አለመሆኑን፤ ይልቁንም የወንዶችም የሴቶችም ተሳትፎ ማጎልበት መሆኑን ከልብ ማመን ይኖርብናል።

ይሁን እንጂ የሴቶችን ተሳትፎ በቀላሉ የምናገኘው ነገር አይደለም። ሴቶችን ለማሳተፍ አስተውሎት የተሞላበት ሥራን ይጠይቃል። የውይይት ርዕሶቻችን፣ የስብሰባ አመራራችን፣ የስብሰባ ቦታ አመራረጣችን ለወንዶች ብቻ ሳይሆን ለሴቶችም የተመቹ መሆን ይኖርባቸዋል። ፓለቲካ የወንዶች ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ በተግባር ማሳየት ይኖርብናል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እህቶችና እናቶች ትግሉን በስፋት እንዲቀላቀሉ ጥሪ ያደርጋል። በንቅናቄዓችንም ሆነ እኛ ተሳትፎ በምናደርግባቸው እንቅስቃቄዎች ውስጥ ለሴቶች ምቹ የሆኑ አደረጃጀቶችን ለመከተል እንሞክራለን፤ ይህንን ደግሞ ያለማቋረጥ ማጎልበት እፈልጋለን። ስለሆነም እህቶችና እናቶች በትግላችን በንቃት ተሳተፉ፤ አብረን እንታገል።

**ሴቶችና ወንዶች፤ ህፃናት፣ ወጣቶችና አረጋዊያን ሁላችንም የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝን በአንድነት "በቃህ!!!" እንበለው።**

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአክል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

### ግብጽ ውስጥ በህዝብ የተመረጠ መንግሥት እስኪመሠረት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በድፍረት እየተናገሩ እንደሆነ ይታወቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ለወያኔ አገዛዝ ቀረቤታ እንዳለው የሚታመነው ሪፖርተር ጋዜጣ "አመቺ ሁኔታን ባለመጠቀምና በማስመለጥ ወደርየለሾች እየሆንን ነው:: ያለፈው ይለፍና በአሁኑ ጊዜ ከግብፅ ጋር የተፈጠረውን አመቺ ሁኔታ እንዳያመልጠን እንጠንቀቅ"፡ በማለት የግድቡ ግንባታው ወሬ በግብጽ ውስጥ የተፈጠረውን አለመረጋጋት ለመጠቀም የታቀደ መሆኑን የሚያሳይ አስገራሚ ጽሁፍ አውጥቶአል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በዓባይ ወንዝ ላይ የሚሠራውን የህዳሴ ግድብ ለማጠናቀቅ «ያስፈልጋል» የተባለው የገንዘብ መጠን፣ የመንግሥት ቅድመ ዝግጅት አለመኖርና የግድቡ ስራ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዉስጥ አለመካተቱ በእቅዱ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ግልጽነትና ተጠያቂነት ተአማኒነት እንደሚያሳጣው ገልጿል።

ይህንን አምርሮ የተነሳን ህዝብ የተቃውሞ አቅጣጫ ለማስቀየር ሆን ተብሎ የተፈበረከ የግድብ ግንባታን አስመልክቶ ከሰሞኑ የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት "የሃይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የተለያዩ ተቋማትና የፖለቲካ ፓርቲዎች የተካተቱበት ብሔራዊ ምክር ቤት አቃቁመዉ "ኢሕአዴግ ለብቻው የሚያደርገው ነገር የለም" የህዳሴዉ ግድብ ሕዝቡ የራሱን ገንዘብ አውጥቶ በራሱ ሊቆጣጠረው የሚችል ፕሮጀክት ነው የሚል ተራ የማጭበርበሪያ ዘመቻ ጀምረዋል:: እዚህ ላይ በጣም የሚገርመዉ እነዚህ በህዝብ ንብረት የከበሩ ባለስልጣኖች የታላቁ ህዳሴ ግድብ በመባል የተሰየመውን ፕሮጀክት ገንዘብ በሙስና ለመብላት ቀርቶ አንድም ሳንቲም ቢሆን መውሰድ አይቻለም ሲሉ መናገራቸዉ ነዉ"። "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ ይህ አባባላቸዉ የሚያሰየነው የመለስ ዜናዊ ስርአት ምን ያህል በሙሰኝነት የተዘፈቀ ዝቃጭ ስርአት መሆኑን ነዉ።

### የተባበሩት መንግስታት ተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በወቅቱ ሊቀርብ ካልቻለ የከፋ ችግር ሊከሰትና በርካታ ሰዎችም ሊሞቱ እንደሚችሉ ከወዲሁ የአደጋ ማሰጠንቀቂያ ሰጥቱአል።

ከዚሁ የርሃብ ችግር ጋር በተያያዘ የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የ 75 ሚሊዮን ዶላር ገንዘብ ርዳታ እንዲደረግለት መጠየቁን ነገር ግን ጥያቄው በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ያሉ ዜጎችን ህይወት መታደግ እንደማይችል የተባበሩት መንግስታት አስታውቁአል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናትና ሆድ አደሮች በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን እንዲህ አይነት ችግር ውስጥ በሚገኙበት ሁኔታ የሃገሪቱን ሃብት በመዝረፍና የግል ጥቅማቸውን በማሳደድ ተግባር ተጠምደው እንደሚገኙ በተደጋጋሚ መዘገባችን አይዘነጋም።

መለስ ዜናዊና አጋፋሪዎቹ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በተከታታይ ላለፉት 7 አመታት በድርብ አሃዝ አድጓል በማለት ሪካሽ ፕሮፖጋንዳ ቢነዙም የህዝባችን በረሃብ አለንጋ መርገፍ ዜና ከአመት አመት እየጨመረ መምጣቱን እላቆመም። ወያኔዎች አገራችን አያደገች ነው በሚሉበት የኢኮኖሚ አሃዝ እያደገ ህዝቡን መቀለብ የተሳነው ኢኮኖሚ ከአገራችን በስተቀር በምድር ላይ እንደሌለ ኢኮኖሚስቶች ይናገራሉ። የወያኔን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለዲያስፖራው ለማስረዳት ተልከው የነበሩት ቱባ ቱባ ባለስልጣናት ከአሁን ቦኋላ ረሃብ በአገራችን ታሪክ ሆኖአል እስከማለት ደርሰው እንደነበር ለመታዘብ ተችሎአል።

### ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የፕሬስ ነጻነትን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ውዝግቡ ሲፈጠር ዋሾዉ በረከት ስምኦንን ጨምሮ በርከት ያሉ ሆድ አደር ባለስልጣናት ተገኝተዉ ነበር። በአዲስ አበባዉ በአል ዝግጅት ወቅት ጽሑፍ እንደሚያቀርብ ምንም ያልተገለጸለት የብሮድካስት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተርና የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት በእለቱ በአል ንግግር ለማድረግ አለመዘጋጀቱን ሳይሸሽግ ለመድረኩ መግለጹ የእለቱ ትልቅ የመነጋገሪያ አርእስት ሆኖ ዉሏል ። በበአሉ የመክፈቻ ስነስርአት ላይ የመንግሥታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ ባን ኪ ሙን የላኩት መልዕክት በንባብ የተሰማ ሲሆን የዋና ጸሐፊው መልዕክት ከስልሳ ዓመታት በፊት የታወጀውን ዓለምአቀፉን የሰብዓዊ መብቶች ውሳኔ የሚያጐላና በተለይም የአንቀጽ ፲፱ኝን መሠረታዊ መብቶች የሚያመለክት መሆኡ ታውቁአል። ጽሁፉ በፕሬስ ነፃነት ላይ የሚፈጸምን ጥቃት በዓለምአቀፍ ህግ ላይ እንደሚፈጸም ጥቃት እንደሚቆጠር አስረድቷል:;

ዘረኛውና አምባገንነኑ የወያኔ አገዛዝ የነጻ ፕሬስን በማፈን ከሚታወቁት ጥቂት አገራት አንዱና ዋነኛው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን የዓለም አቀፍ የነጻ ፕሬስ በአልን በመመርኮዝ ጋዜጠኞች ሃሳባቸውን በነጻ እንዳይገለጹ ለማድረግ የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት በእለቱ ያሳዩት እኩይ ተግባር ለታዘቢዎችም አሳፋሪ እንደነበር ብዙዎቹ የስብሰባው ተሳፋታፊዎች ሳይሸሽጉ ተናግረዋል።በእለቱ ስብሰባ ከ160 በላይ ጋዜጠኞች በስብሰባው ላይ የተገኙ ቢሆንም በተፈጠረው ውዝግብ የተበሳጩ በርካቶች አዳራሹን እየለቀቁ ሲሄዱ ታይተዋል።

በእለቱ ስብሰባ የተሳተፉት የአውራምባ ታይምስ ማኔጂንግ ኤዲተር አቶ ዳዊት ከበደም የቀኑን አስገራሚነት በመግለጽ «የፕሬስ ነፃነት ቀን ሲከበር የሚመለከታቸው አካላት እያሉ ፕሬስን በማፈን የሚታሙ ሰዎች አብረን እናክብር ማለታቸው ሳያንስ ይህንን የመሰለ ቀን ለማፈን ሞክረዋል፤» በማለት ዘረኛው አገዛዝ ለግሉ ፕሬስ ያለውን አመለካከትና የሚያካሂደውን አፈና ያሳየበት ቀን እንደነበር መናገራቸውንም ለአገዛዙ ቅርበት ያለው ሪፖርተር ጋዜጣ ጭምር እንደዘገበዉ ታዉቋል።

## የዴሞክራሲ ትግሉ በኢትዮጵያ: የማጥቃት ስልቶቻችን

### ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአትላንታ በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ ያደረጉት ንግግር አፕሬል 23 2011 (ክፍል 2)

የግብጽ መጣብህ ወሬ በሙከራ ላይ እያለ መለስ ሌላ ጭቃ ወረወረ: የህዝቡን ስሜት ለመለካት:: በዚህኛው ደግሞ ዋናው ተዋናይ የተለመደችው ኤርትራ ሆና ኣሁን ግን መልእክቱ "የኛ ትእግስት ስላለቀ እኛ በጉልበት የኤርትራን መንግስት እንቀይራለን" የሚል ሆነ:: ምነው? ሲባል "ተቃዋሚዎቼን ይረዳሉ" ኣለ:: እንዴ ታዲያ ይሄ ጦርነት ለመግጠም በቂ ምክንያት እንዴት ይሆናል? ኣንተስ የሱን ተቃዋሚዎች በግላጭ ትረዳ የለም ወይ? ለሚለው ጥያቄ ምንም ኣጥጋቢ መልስ የለም:: ውስጥ ለውስጥ ግን በካድሬዎቹ ኣማካይነት "ኣሁን ጉዳያችንን ጨርሰን ነው የምንመለሰው፤ ኣሰብንም እናስመልሳለን" የሚል ወሬ በሰፊው ማስነገር ጀመረ:: በጎን ደግሞ በተቃዋሚዎች ሬድዮ ላይ ለኤርትራውያን በትግርኛ ባስተላለፈው መልእክት እሱ የኤርትራ ነጻነት ዋና ደጋፊ እንደሆነ፤ በዚህም እንደሚኮራ:: ኣይደለም ኣሰብን ማስመለስ የሱ መንግስት በኣለም ኣቀፉ ውሳኔ መሰረት ባድመንም ሆነ በኢሮብ የሚገኘውን መሬት ለኤርትራ እንደሚመልስ የሚገልጽ ቃለምልልስ ሰጠ:: ትግርኛ ለማይሰማው የኣገሩ ህዝብ ግን ኤርትራን ለመውጋትም ሆነ ኣሰብን ለማስመለስ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የወታደር ምልመላ እንቅስቃሴ ተጀመረ ተባለ:: ነገሩን ግን ያለም ኣቀፉ ማህበረሰብም ሆነ ያገሩ ሰው እንዳልተዋጠለት ሲረዳ ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ "ኣይ ይህ ማለት እንወራለን ማለት ኣይደለም፤ ይልቁንም በትንሹ ስንረዳቸው የነበሩትን የኤርትራ ተቃዋሚዎች ኣሁን በሰፊው እንረዳለን ለማለት ነው" ሲል ቀላመደ:: ይህ ለምን ወሬ ሊሆን እንደሚችል ግን ግልጽ ኣይደለም::

እነኝህ ሁለት ማስቀየሺያዎችም ቢሆኑ በቂ ቀልብ ኣልሳቡም:: ከኣንድ ከሁለት የዜና ሳይክል ያለፈ የህዝቡን ቀልብ ቆንጠጠው ለረጂም ጊዜ ሊይዙት ኣልቻሉም:: በዚህን ጊዜ ነው ኣለኝ የሚለውን የመጨረሻ ካርድ የመዘዘው:: በኢትዮጵያውያን ስሜትና ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለውን: ብዙ ዘፈኖች የተዘፈኑለትን: የኣባይን ወንዝ መገደብ ጉዳይ ከኪሱ ኣውጥቶ የፖለቲካ ጨዋታው ውስጥ የወረወረው:: የነመለስን ኣይንኣውጣነት በቅጡ ያልተገነዘቡ ወገኖች ይህንን የመሰለ ከፍተኛ የኣገር ጉዳይ ኣንድን ኣገር እንመራለን በሚሉ ሰዎች እንዲያው በደንብ ሳይታሰብበት ለጊዜያዊ የፖለቲካ ቁማር መጠቀሚያ ያውሉታል ብሎ ለማመን ሲቸገር ይታየኛል:: በዚህም ምክንያት የተወሰኑ ሰዎችን (በተለይም ኣውቀው መታለል ለሚፈልጉና እንደ ኤርትራው ጦርነት ጊዜ ኣጋጣሚውን ከመንግስትጋ ለመጠጊያ ሊጠቀሙበት ለሚፈልጉ) ሲያነሆልል ይታየኛል:: ነገር ግን መለስ ባለፉት 20 ኣመታት በኢትዮጵያ መሰረታዊ ሀገራዊ ጥቅሞች ላይ ሲቆምር በጥሞና ለተከታተለ፤ ይህ በፍጹም ሊገርመው ኣይገባም:: ቢገርመው የሚገርመው ኣሁንም በዚህ የሚታለሉ ሰዎች ኣሉ ብሎ መገመቱ ብቻ ነው የሚሆነው:: በዚህ ደረጃ ምን ያህል ኣይነደረቅ እንደሆኑ ለማሳየት ኣንድ በሰፊው የሚታወቅ ምሳሌ ጠቅሼ ልለፍ::

የኢትዮጵያና የኤርትራ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔውን እንዳሳለፈና ማንበብ ለፈለገ ሁሉ በኢንተርኔት ካሰራጨ በሁዋላ በጊዜው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ስዩም መስፍን የኢትዮጵያን ህዝብ "እንኳን ደስ ኣለን፤ የጠየቅነውን ብቻ ሳይሆን ያልጠየቅነውን መሬት: ባድመን ጨምሮ ለኛ ተወሰነልን": የሚል መግለጫ በመገናኛ ብዙሀን ሰጠ:: በጊዜው በኣገር ውስጥ የሚታተሙ የግል ጋዜጦች: የለም ይህ ውሳኔ እንደዚያ ኣይልም: ባድመ ለኤርትራ ነው የተወሰነው ብለው ውሳኔውን ተርጉመው ቢያቀርቡም የመለስ መንግስት "የሌባ ኣይነደረቅ" እንዲሉ ያልሆነውን ሆነ ብሎ ባደባባይ ከመናገር ኣልፎ ይባስ ብሎ ህዝቡን ደስታህን ኣደባባይ ወጥተህ ግለጽ ብለው የድጋፍ ሰልፍ ኣስወጡ:: ይህ ኣሳዛኝ ድርጊት ከተፈጸመ ከኣምስት ኣመት በኋላ በምርጫ 97 ወቅት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን በሚመለከት ለክርክር በቀረብንበት ጊዜ ይህንን ጉዳይ ለስዩም ኣነሳሁበት:: በቀጥታ ለህዝብ በሚተላለፍ የቴሌቪዥን ሰርጭት ላይ እንደገና ባድመ በፍርድ ቤቱ የተወሰነው ለኛ ነው ብሎ ሽምጥጥ ኣድርጎ ዋሸ:: መለስ በበኩሉ ላገኘው የውጭ ባለስልጣን በሙሉ (ባለፈው ሁለት ሳምንት ለኤርትራውያን በትግርኛ ሬድዮ እንደተናገረው) "እኔ ባድመ ለኤርትራ እንዲመለስ እፈልጋለሁ የትግራይ ብሄረተኞች ኣስቸግረውኝ እንጂ" እያለ በሌላ በኩል እንደሚናገር ይታወቃል::

እንደ ኢትዮጵያ ኣቆጣጠር በ1993 ዓ:ም መለስ ዜናዊ ካይሮ ድረስ ሄዶ ከሙባረክ ጋር "ኢትዮጵያም ሆነች ግብጽ የኣባይን ወንዝ የውሀ ፍሰት የሚቀንስ ምንም እርምጃ ኣይወስዱም" የሚል ስምምነት ተፈራረመ:: ኸረ ይህ ስምምነት በጎ ኣይደለም የሚልን ኣገር ወዳድ ሁሉ ጦር ሰባቂ፤ ትምክህተኛ ተብሎ ሲዘለፍ ነበር:: ታዲያ ዛሬ የኣባይ ወንዝ ግድብ ጉዳይ እንደ ትልቅ ኣገራዊ ኣጀንዳ በዚሁ ምንም ባልተቀየረ ሰው መነሳቱ ምንም እውነተኛ የልማት ኣላማ የሌለው ተራ ኣቅጣጫ ማስቀየሻ: ሲያልፍም ከህዝቡ ገንዘብ መዝረፊያ ተራ የውንብድና ስራ መሆኑን ለማሳየት በጣም ትልቅ ምርምር ኣይጠይቅም:: በመጀመሪያ መለስ ራሱ ጠበቅ ኣድርጎ ሲጠየቅ "ምንም ባይሳካም እንኩዋን መሞከሩ ጥሩ ነው" ነበር ያለው:: መቼም ሰማንያ ቢልዮን ብር የሚያወጣ ፕሮጀክት ኣይደለም ሰማንያ ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ፕሮጀክት እንኳን በኣዋቂዎች ኣስር ጊዜ ኣዋጭነቱ ከተለያየ ኣቅጣጫ ተመርምሮና ተረጋግጦ ነው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚኬደው:: ሁለተኛ የመለስ ኣገዛዝ ኣገሪቱን ወደ መካከለኛ ገቢ ደረጃ በኣምስት ኣመት ጊዜ ውስጥ ያሸጋግርልኛል ብሎ: በብዙ ባለሙያዎች የተጠና ያለውንና ግን በምን ገንዘብ እንደሚሰራው ምንም የማይገልጸውን "የኣምስት ኣመቱን የትራንስፎርሜሽን እቅድ" ካወጀ ገና 6 ወራት ቢሆኑት ነው:: በዚህ ኣስደናቂ እቅድ ላይ ኣባይ የሚባል ግድብ ኣይደለም ስሙም የለም:: ኣባይ ለመለስ የተገለጸለት ከእቅዱ በኋላ ነው ማለት ነው? ከዚያ በፊት ኣባይ የት ሄዶ ነበር? እሺ ዘግይቶ እንኳን ቢገለጽለት: ምነው ትንሽ ዘርዘር ያለ ጥናት ቢጤ በመጀመሪያ ኣያስጠናም ህዝቡን ገንዘብ ኣዋጡ ከማለትና በጣም ብዙ ገንዘብ ኣውጥቶ ከ50 በላይ ከፍተኛ ካድሬዎቹን ለሽያጭ ስራ ከመላኩ በፊት? እነኝህን ሰዎች የላከበት ገንዘብ እኮ መነሻ ጥናት ለማስጠኛ የማያንስ ወጪ ነው! ሶስተኛ መለስ እኮ በመንግስቱ ጊዜ የተሰሩ ግድቦችን ተግባራዊ እንዳይሆኑ ሆን ብሎ እንቅፋት ሲሆን የነበረ ሰው ነው:: በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ (በዛሬ ብር ወደ 3 1/2 ቢሊዮን ያክል) ወጥቶበት በጣልያኖች የተሰራውንና የኣገሪቱን የእርሻ ምርት ከ10% በላይ ይጨምራል የተባለ ግድብ መና ኣስቀርቶ: ጣሊያኖች እኛ በገንዘባችን ስራ እናስጀምረው ብለው ሲለምኑት እምቢ ብሎ በስፍራው የተሰሩትን የመሰረተ ልማት ኣውታሮች ነቃቅሎ ያስፈረሰ "የልማት ጀግና" ነው! በጋምቤላ ክልል የተሰራውን የኣልዌሮን ግድብ በተመሳሳይ መልኩ እንዳይሰራበት ያደረገ ሰው እኮ ነው:: መለስ እኮ ስልጣን ላይ ሲወጣ በኣባይ ላይ የሚሰሩ የኣገሪቱን ባለሙያዎች ሁሉ ኣባሩልኝ ብሎ ከስራ ኣባሮ ለስደት የዳረገ መሰሪ ሰው ነው:: ዛሬ ስለ ኣባይ: ያውም ያለምንም ጥናት: ልገድብ ነው ሲል የሚታመነው በምን ሂሳብ ነው? ምን ያህል ጅል ብንመስለው ነው? ወይንስ እኔ እንደምገምተው ጭንቀት የወለደው ትርምስ?

እስኪ ለኣንድ ደቂቃ መለስን እስከ ዛሬ በሰራው ሳይሆን ከኣሁን በኋላ እሰራለሁ በሚለው እንመዝነው እንበል: ያ ከታማኝ ጋር ቪኦኤ ላይ የተከራከረው ካድሬ እንዳለው:: መለስ እስከዛሬ ሲያደርግ የነበረውን ጥፋት ኣምኖና ተጸጽቶ ከኣሁን በሁዋላ ልማት ለማምጣት ወስኖኣል:: መለስ የተቀየረ ሰው ነው እንበል:: ይህም ከሆነ እሰዬው ነው:: ግን የተቀየረ ከሆነና እውነትም ለኣገሪቱ ልማትን ከተመኘ ብዙ ወጪ ሳያስወጣ ልማት የሚያመጡ ብዙ ነገሮችን በቀላሉ ማድረግ ይችላል:: በኢኮኖሚክስ ትምህርት ትልቅ ስምምነት የተደረሰበት ኣንድ ግኝት ልማት የሚመጣው በነጻነት ማሰብ የሚችል ህዝብ ባለበት: መልካም ኣስተዳደር በሰፈነባቸው: ኣገሮች መሆኑን ነው:: መልካም ኣስተዳደር ማለት ደግሞ ከሙስና የጸዳ: የማህበርሰቡ ተጠያቂነት ያለበት: ነጻ ሚዲያ ያለበት: የህግ የበላይነት የሰፈነበት ኣገር ማለት ነው:: መለስ ለኢትዮጵያ ካሰበ እነኝህን ነገሮች ሳንቲም ሳያወጣ በኣንድ ፊርማ ማድረግ ይችላል:: ግን ይህን መቼም ኣያደርግም:: ይልቁንም ስለኣባይ በሚሰብክበት በኣሁኑ ጊዜ በኣገር ውስጥ እያደረገ ያለው ነገር ከዚህ ፍጹም ተቃራኒውን ነው::

ከፍተኛ ካድሬዎቹን ውጭ ኣገር ለስብሰባ በላከበት ከሁለት ሳምንታት በፊት የቀበሌ ወጣቶችና ሴቶች ማህበራት ኣባላቱን ሰብስቦ ከኣሁን በኋላ ሁሉም ሰው እንግዳ ቤቱ ካሳደረ ለቀበሌ ማስመዝገብ እንዳለበት መመሪያ ሰጠ:: ደርግ እንኳን ሞክሮ ያልተሳካለት ኣፈና:: ባለፉት ሁለት ሳምንታት ብቻ በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች ያውም በህዝብ ተመርጠው የነበሩ እንደራሴዎችን ያለምንም ጠያቂ ዘብጥያ ወርደዋል:: በሚዛን ቴፒ ተማሪዎች ላይ የተወሰደው ጨካኝ የግድያ እርምጃ: በዚህ ሁለት ሳምንት ውስጥ ነው የተካሄደው:: ባለፈው ሳምንት ከተለያዩ የኣገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች በሌሊት እየታፈኑ የተወሰዱትና የት እንደደረሱ ያልታወቁ የኦሮሞ ተማሪዎች "ከኣባይ ልማት ጋር በጋራ የሚደረጉ" የልማቱ ኣስፈላጊ ግብኣቶች ነው የሚመስሉት:: ሙብት ከልማት በሁዋላ የሚለው ጊዜ ያለፈበት ፈሊጥ በዛሬው ኣለም እንደማያዋጣ ያለመረዳት ኣስከፊ የመሸበት ስህተት ነው:: ከዚህ ሁሉ ደግሞ በከፋ መልኩ የሚታየው ማህበረሰቡን ለመከፋፈል የሚከተለው ዘይቤ ነው:: ኦሮሞዎችን ለብቻቸው ጠርቶ "ኣዲስ ኣበባን ፊንፊኔ ብለን እንሰይማታለን ከሌላው ጋር ኣትተባበሩ" ሲል፤ ሌላውን ደግሞ "ኦሮሞዎች ኣገሪቱን ሊገነጥሉ ነው ኣትተባበሩዋቸው" እያሉ በካድሬዎች ማስወራት:: ፖሊስ ዝም ብሎ እያየ በክርስቲያንና በሙስሊሙ መሀል በቅርቡ በጅማ ዞን እንደሆነው ግጭት ሲፈጠር ኣውቆ ኣለመከላከል:: ይህንን ነው እንግዲህ "የኣባይ ልማት የመጀመሪያ ክፍያ" (down payment) ኣድርገን እንድንቀበለው የሚነግረን:: ስለዚህ የኣባይ ግድብ ወሬ ልማትን ኣስቦ የተነሳ ወሬ ኣይደለም::

ልማትን ኣስቦ የተነሳ ወሬ ካልሆነ እንግዲያው ምን ሊሆን ይችላል? ከላይ እንዳልኩት የማህበረሰቡን ቀልብ ከለውጥ ፍላጎት ለማስቀየሺያ የታሰበ ነው:: የኣባይ ጠንካራ ስሜታዊ ስበት (imotional appeal) በሁለት መክንያቶች የማስቀየሻ ኣላማውን ያሳካልኛል ብሎ ያመነ ይመስላል:: ኣንደኛ በኣገር ውስጥ ማህበረሰቡን እያስመረረ ያለው የኑሮ ውድነት (በዚህ ወር ብቻ በመንግስት በራሱ ኣሀዝ የዋጋ ግሽበት 25% ገብቶኣል) በኣካባቢ ኣገሮች ከታየው "የለውጥ ይቻላል" ልበ ሙሉነት ጋር ተባብሮ ስልጣኑን ክፉኛ ሊፈታተነው እንደሚችልና ነገሩም ከተጀመረ እንደቀደሙት ጊዜያት በጉልበት ብቻ ሊወጣው እንደማይችል በመረዳት ሳይጀምር በእንጭጩ ለማስቀረት:: ሁለተኛ በኣገር ውስጥ የሚካሄደው እንቅስቃሴ በውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ መታገዙ ለስኬቱ ወሳኝ ነው ብሎ ስለሚያምን በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ ለመከፋፈያ: በተለይም የኣገር ፍቅር ያማለለውን የዋህ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛ ሊታገለው ቆርጦ ከተነሳው "ኣክራሪ ዳያስፖራ" ለመለየት በዚህም በኣገር ውስጡ ወጣት ይነሳል ብሎ የሚጠብቀውን የለውጥ እንቅስቃሴ ነጥሎ ለመምታት የታለመ ይመስላል::

### 3. በህዝቡ ውስጥ የሚታየው ስሜት

በኢትዮጵያ ለውጥ የመነሳቱን ሁኔታ ከሚወስኑት ጉዳዮች ኣንዱ ማህበረሰቡ ለዚህ ማስቀየሻ የሚሰጠው ምላሽ ነው:: ይህንንም በሚመለከት ከሰሜን ኣፍሪካው ኣብዮት ጀምሮ መለስ ለሚወስዳቸው እርምጃዎች በኣገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የሰጠው ምላሽ የነመለስ ፕላን እንዳልሰራና እንደማይሰራ ነው የሚያሳየው:: ኣገር ውስጥ ባለው ህዝብ ብንጀምር: ከኤርትራ ጋር ስለሚደረገው ጦርነትና ኣሰብን ስለማስመለስ የሚወራውን ወሬ በኣርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ በቅርብ የተበተነው ወረቀት እንዳለው "እስኪ በመጀመሪያ በባድመ፤ በሶማልያና በሌሎቹም የመለስ ጦርነቶች የሞቱትን ወገኖቻችንን ብዛትና ስማቸውን ለህዝቡም ሆነ ለቤተሰባቸው ንገርና፤ ከዚያም በነሱ መሞት ቤተሰቦቻቸው እርማቸውን ያውጡና: በነኝህ ጦርነቶች ኣገራችን ያገኘችውን ጥቅም ንገረንና ከዚያ በኋላ ስለመጪው ግጭት ጠቃሚነት እናወራለን" ነው:: ስለ ኣባይ ግድብ የተሰጠው መልስ (በኢትዮጵያ እያደገ ከመጣው የውስጥ ለውስጥ ሚዲያ (underground press) በተረብ መልክ የተነገረው "መጀመሪያ የገደብከውን ልሳናችንን፤ የገደብከው ሆዳችንን ፍታና ስለሌላ ግድብ እናወራለን፤ በሰማይ ላይ ስላለው ላም ከምታወራልን በኣይናችን የምናየው፤ በእጃችን የምንጨብጠውና በቀላሉ ልንደርስበት የምንችለውን ለውጥ ስጠን" ነው ያሉት::

(ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከኢትዮጵያዊያን ገንዘብ ለመዝረፍ የቤት ለቤት ቅስቀሳ ሊጀምር መሆኑ ተዘገበ

የዘረኛው ወያኔው ኢህአዴግ በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ ካድሬዎቹንና አባላቱን በሕዝብ ንቅናቄ አመራር ክህሎት ላይ ሊያሰለጥኑለት የሚችሉ የተመረጡ ካድሬዎቹን የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠቱን የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ጽ/ቤት የዜና ምንጮቹን በመጥቀስ ኢሳት ዘገበ፡፡ የአሰልጣኞቹ ሥልጠናም ያለፈው እሁድ ሚያዚያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ መጠናቀቁን ዘገባው ጨምሮ ገልጹአል፡፡

እንደ ኢሳት ዘገባ ሠልጣኝ የኢህአዴግ ካድሬዎች በክፍለ ከተማ፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙትን ካድሬዎችና የተመረጡ የኢህአዴግ አባላትን በቅርቡ የሚያሰለጥኑ ሲሆን ዓላማውም በመላ ኢትዮጵያ አንድ አይነት ሕዝባዊ ንቅናቄ በመፍጠር ሕብረተሰቡ በዓባይ ወንዝ ላይ የሚገነባውን ህዳሴ (ሚሊኒየም) ግድብ ላይ አትኮሮቱን አሳርፎ ሁሉም ዜጋ ሌላ ነገር እንዳያስብ ማድረግ ነው ብሉአል፡፡

በመጪዎቹ ቀናት አብዛኛዎቹ የኢህአዴግ ካድሬዎችና የተመረጡቱ አባላት ይህን የሕዝብ ንቅናቄ አመራር ክህሎት ሥልጠና ያገኛሉ ያሉት የኢሳት ምንጮች ከዚያ በኋላ እንደ ምርጫ ዋዜማ ቅስቀሳ ቤት ለቤት፣ በንግድ ሱቆችና የግል ድርጅቶች እየተንቀሳቀሱ ድጋፍ ያሰባስባሉ ተብሉአል፡፡ የዘረኛው አገዛዝ መሰሪ አላማ ቦንድ የገዛውን፣ ሥጦታ የለገሰውንና በምንም ደረጃ በግድቡ ግንባታ ላይ ያልተሳተፈውን ግለሰብ፣ ቤተሰብና ተቋማት የመለየት ሥራ በማከናወን በአባይ ግድብ ስራ ሥራ ላይ ሰዎቹንና ተቋማቱን የማስገደድ ሥራ ይሰራሉ ተብሉአልል፡፡

ዘረኛው የወያኔ አምባገነንና አፋኝ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን በኑሮው ውድነት፣ በከፍተኛ ሁኔታ እየተማረሩ በመጡበት በአሁኑ ሰአት የአባይን ግድብ ፕሮጀክት ድንገት በማምጣት የህብረተሰቡን የትኩረት አቅጣጫ ለመቀየር ጥረት እያደረገ በማድረግ ስራ ላይ ተጠምዶ ይገኛል።

## በአባይ ግድብ ግንባታ ስም የዜጎችን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ወያኔ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ጋር ለመፍጠር ጽ|ቤታቸው ድረስ በመጓዝ ከአመራር አባላቱ ጋር ውይይት ለማድረግ እንደሞከረ ታውቆአል። የግርማ ብሩ ጥረት በዚህም ሳያበቃ ባለፈው ቅዳሜ ሚያዚያ 22 የሲቪሊቲ ፓልቶክ ሩም በመባል በሚታወቀው አፍቃሪ ወያኔ ግለሰቦች የውይይት መድረክ ውስጥ ገብቶ ከ3 ሰዓት በላይ የፈጀ ቃለመጠይቅ እንዳደረገና በዚያው ዕለት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰለ እምነታቸውና ስለ አገራቸው ከሚወያዩበት ኢትዮ ሚስሊምስ ኢነተርፌየዝ ዲያሎግ ፎር ጀስትስ ከሚባለው የፓልቶክ መድረክ ገብቶ ከ4 ሰዓት በላይ በፈጀ ቃለመጠይቅ የጌቶቹን የተሳሳተ የኢኮኒሚ፤ የፖለቲካና ማህበራዊ ፖሊሲዎችን ሲያስተባብል ቆይቶአል።

ግርማ ብሩ በተለይ በኢትዮ ሙስሊም ኢንተርፌይዝ ባልቶክ ውስጥ በህይወቱ ሙሉ ገጥሞት የማያውቀው ክርክር እንደገጠመውና እወክለዋለሁ የሚለውን አገዛዝ ወንጀሎች ማስተባበል ተስኖት በቃላቶች አጥረት አፉ ስምታታና ነፍሱ ከስጋው ጋር ስትሟገት እንደዋለች በመድረኩ ውስጥ የተደረገውን ክርክር የተከታተሉ የዝግጅት ክፍላችን ባልደረቦች ታዝበዋል።

አፍቃሪ ወያኔ በሆነው የሲቪሊቲ ሩም ጥያቄና መልሱን ለመታዘብ እና ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ የገቡትን ጨምሮ 250 የሚሆኑ ሰዎች የተከታተሉ ሲሆን ተጋባዥ እንግዶች ሲኖሩት ከ500 የቤቱ የማስተናገድ አቅም በላይ እድምተኞች የሚረባረቡበት የኢትዮ ሙስሊ ኢንተርፌይዝ መድረክ በ ዕለቱ ያስተናገደው ከዘወትር ደንበኞች ቁጥር እጅግ ያነሰ እንደነበር ይሄውም እስከ 350 እድምተኞች ብቻ እንደታዩበት ክርክሩን የተከታተሉት ዘጋቢዎቻችን አረጋግጠዋል።

## በአማራ ክልል አንድ ወታደር ራሱን ጨምሮ አራት ሰዎችን በፈንጅ መግደሉ ተሰማ

በአማራ ክልል ፋግታ እየተባለ በሚጠራው ወረዳ ልዩ ስሙ አዲስ ቅዳም በተባለ አነስተኛ ከተማ አንድ ወታደር ራሱና በቦርድ የተገለለ ሌላ ወታደር ጨምሮ አራት ሰዎች መግደሉን ባህርዳር ከተማ የሚገኘው ዘጋቢያችን ከስፍራው የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ ዘገበ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ወታደሩ ይህን ርምጃ ለመውሰድ የተገደደበት ዋናው ምክንያት በሃገሪቱ ብሎም በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያለው የተበላሸ አሰራር አንገሽግሾት እንደሆነ የአካባቢው ሰው የገለጹለት መሆኑን በመጥቀስ አስታውቆናል። በዚሁ የቦምብ ፍንዳታ ከሞቱት አራት ሰዎች ውጪ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ የታወቀ ነገር አለመኖሩን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና በደል በመከላከያ ሰራዊቱም ላይ ዋነኛ ችግር መሆኑ በስፋት የሚታወቅ ሲሆን በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ያለው የተበላሸ አሰራር ሰራዊቱ መከላከያን በየጊዜው እየጣለ እንዲወጣ እንዲሁም የጦር መሳሪያዎችን በመሸጥ ኑሮውን እንዲደጉም እየተገደደ እንደሆነ ለዘጋቢያችን አስተያየት የሰጡ የአካባቢው ነዋሪዎች ገልጸዋል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሰራዊት አዛዦች በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ አካብተውና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እጅግ ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶችን እየሰሩ ባለበት ሰአት ተራው ወታደር ለቤተሰቦቹ የሚልከው ገንዘብ አጥቶ እንደሚቸገር የመከላከያ አባላት በተደጋጋሚ መግለጻቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## አዲስ አበባ ውስጥ ያለው ውጥረት እየተባባሰ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በንዲህ እያለ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የኑሮ ውድነት እጂግ በአስደንጋጭ ሁኔታ ወደ ከፋ ደረጃ እየተሸጋገረ መሆኑንም ዘጋቢያችን አያይዞ ከላከልን መረልጃ ለማወቅ ተቺሉአል። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በቅርብ ቀን የአንድ ኩንታል ሲሚንቶ ዋጋ በአንድ ጊዜ የ126 ብር ጭማሪ ማድረጉን ለዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቅርበት ያለው ሪፖርተር ጋዜጣ እሁድ እለት ባወጣው ዘገባ ላይ ይፋ ማድረጉን ገልጹአል።

ኢትዮጵያዊያን በንዲህ አይነት ፈተና ውስጥ ባሉበት አስከፊ ወቅት ዘረኛውና አፋኙ ወያኔ አሁንም ህዝብን ማደንቆሩን እንደቀጠለ የሚታወቅ ሲሆን በተለይም ከቅርብ ቀናት ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ከአባይ ውጪ ምንም የሚወራ ነገር አለመኖሩን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዳንኪራውና ጡሩምባው ሰማይ ምድሩን እያጨናነቀው መሆኑም ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቱአል።

ዘረኛውና መሰሪው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ባለፉት የሃያ ዓመታት የግፍ አገዛዝ ዘመኑ በተደጋጋሚ ውጥረትት ሲገጥመው የቆየ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊያንን፣ በአንድ በኩል በማስፈራራት፣ በሌላ በኩል ነጻ መረጃ እንዳያገኙ የተለያዩ ነጽ ሚዲያዎችን በማፈን፣ ከዚያም ባለፈ መልኩ የኢትዮጵያዊያንን የሃሳብ አቅጣጫ ማስቀየሻ አደናጋሪ ተግባራትን ሲፈጽም እንደቆየና በመፈጸምም ላይ እንደሚገኝ በስፋት ይታወቃል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org